# የአማራ ክልል ምክር ቤት ዶክተር አምባቸው መኮነንን ርዕሰ መስተዳድር አድርጎ ሾመ



ባህርዳር የካቲት 29/2011 የአማራ ክልል ምክር ቤት  አምስተኛው ዙር አራተኛ ዓመት የስራ ዘመን 12ኛ መደበኛ ጉባኤ ዶክተር አምባቸው መኮነንን የክልሉ ርዕሰ መስተዳደር አድርጎ በመሾም ተጠናቀቀ፡፡

የምክር ቤቱ ጉባኤ ዶክተር አምባቸውን የሾመው  የክልሉ ርዕሰ መስተዳደር የነበሩት አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ያቀረቡትን የመልቀቂያ ጥየቄ ከተቀበለ በኋላ ነው፡፡

አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ላለፉት አምስት ዓመታት ክልሉን በርዕሰ መስተዳደርነት ሲመሩት ቆይተዋል፡፡

በመሪነታቸውም ወቅት የክልሉን ህዝብ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ መስኮች ተጠቃሚ ለማድረግ ሲተጉ መቆየታቸው ተገልጿል፡፡

ለውጡን  ከሚፈልገው አመራር በተሻለ ብቃት ለመምራት መተካት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የምክር ቤቱ ጉባኤ በምትካቸውም ዶክተር አምባቸው መኮንን ርዕሰ መስተዳደር ሆነው እንዲያገለግሉ ሾሟቸዋል፡፡

ዶክተር አምባቸው ከዚህ ቀደም በተለያየ አመራርነት በመሾም ያገለገሉና በኃላፊነት በሰሯቸው ቦታዎችም አመርቂ ውጤት ያስመዘገቡ መሆኑ ታውቋል፡፡

አዲሱ ርዕሰ መስተዳደርም በጉባኤው ፊት ቀርበው ቃለ መሃላ ፈጽመዋል፡፡

በባህርዳር ከተማ የካቲት 26/2011ዓ.ም. ጀምሮ ሲካሄድ የቆየው የክልሉ ምክር ቤት ጉባኤ ከርዕሰ መስተዳድር ሹመት ሌላ የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ ላይ ያለውን ስልጣንና ተግባር ማሻሻያ እንዲሁም የምሁራን መማክርት ማቋቋሚያ ቻርተር ማጽደቂያ አዋጆችን በማጽደቅ ዛሬ ተጠናቋል፡፡